# ትምህርት 41

1. እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ለሰዎች የሚናገረው ለምንድን ነው?

*ሀ- ሰዎች እንዲድኑ።*

2. እግዚአብሔር ዮናስ ወደ ነነዌ ከተማ እንዲሄድ የፈለገው ለምን ነበር?

*ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር የነነዌን ሕዝብ ስለወደደ ነው።*

*ለ- ምክንያቱም እግዚአብሔር የነነዌን ሕዝብ ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ሊያድናቸው ስለ ፈለገ ነው።*

3. ዮናስ የኮበለለው ለምን ነበር?

*ሀ- ዮናስ የኮበለለው ወደ ነነዌ ከተማ መሄድ ስላልፈለገ ነው።*

4. ዮናስ ወደ ነነዌ ለመሄድ ያልገለገው ለምን ነበር?

*ሀ- ምክንያቱም የነነዌ ሕዝብ በጣም ክፉዎች ስለ ነበሩ ነው።*

*ለ- ምክንያቱም የነነዌ ሰዎች የእስራኤላውያን ጠላቶች ስለ ነበሩ ነው።*

*ሐ- ምክንያቱም ዮናስ እግዚአብሔር የነነዌን ሰዎች እንዲያድናቸው ስላልፈለገ ነው።*

5. ዮናስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መኰብለል ችሎ ነበር?

*ሀ- አልቻለም።*

6. ዮናስ ከእግዚአብሔር መደበቅ ችሎ ነበር?

*ሀ- አልቻለም።*

7. ዮናስ ከእግዚአብሔር ማምለጥ ችሎ ነበር?

*ሀ- አልቻለም።*

8. ዮናስ በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ ወደ ነነዌ ስላልሄደ፥ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ሀ- እግዚአብሔር ዮናስን እንዲውጥ ትልቅ ዓሣ ላከ።

9. ዮናስ በትልቁ ዓሣ ሆድ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ቆየ?

ሀ- ለሦስት ቀንና ለሦስት ሌሊት።

10. ዮናስ ከትልቁ ዓሣ ሆድ ውስጥ ራሱን ማዳን ችሎ ነበር?

ሀ- አልቻለም።

11. ዮናስን ማዳን የቻለው ብቸኛው ማን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

12. ሰዎች ከዮናስ ጋር የሚመሳሰሉት በምንድን ነው?

ሀ- ዮናስ ከትልቁ ዓሣ ሆድ ውስጥ ራሱን ማዳን እንዳልቻለ ሁሉ ሁሉም ሰዎች ራሳቸውን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ማዳን አይችሉም።

ለ- እግዚአብሔር ብቻ ዮናስን ማዳን እንደ ቻለ ሁሉ ሰዎችን ሁሉ ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

13. ዮናስ በእግዚአብሔር ላይ ማመፁንና ኃጢአት መሥራቱን በተረዳ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ሀ- እግዚአብሔር ትልቁ ዓሣ ዮናስን በደረቅ መሬት ላይ እንዲተፋው አደረገ።

14. እግዚአብሔር ዮናስን ካዳነው በኋላ «ወደ ነነዌ መሄድ የለብህም» ብሎታል?

ሀ- አላለውም።

ለ- እግዚአብሔር አይለወጥም።

ሐ- እግዚአብሔር በፍጹም አይለወጥም።

መ- እግዚአብሔር አሁንም ዮናስ ወደ ነነዌ እንዲሄድ ይፈልጋል።

15. የነነዌ ሕዝብ ዮናስ የነገራቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ሰሙ?

ሀ- አዎን።

16. እግዚአብሔር መልእክተኞቹ እንዲሆኑና መልእክቱን እንዲነግሩ የመረጣቸው ሰዎች ምን ይባሉ ነበር?

ሀ- ነቢያት።

17. ነቢያት ለሕዝቡ ምን ተናገሩ?

ሀ- የኃጢአትን መንገድ እንዲተውና የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ።

18. ዐሥሩ የእስራኤል ነገዶች የኃጢአት መንገዳቸውን ትተው የእግዚአብሔርን መንገድ ካልተከተሉ ምን ይደርስባቸዋል?

ሀ- እግዚአብሔር ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶች አሸንፈው ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው አሦራውያንን ይልክባቸዋል።

19. በይሁዳ ያሉት ሁለቱ ነገዶች የኃጢአት መንገዳቸውን ትተው የእግዚአብሔርን መንገድ ካልተከተሉ፥ ምን ይደርስባቸዋል?

ሀ- እግዚአብሔር ሁለቱን ነገዶች አሸንፈው ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው ባቢሎናውያንን ይልክባቸዋል።

- እግዚአብሔር አዳኝ እልካለሁ ካለ ብዙ ዓመታት ስላለፉ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ረስቶአል ማለት ነው?

- አይደለም።

- እግዚአብሔር አዳኝን እንደሚልክ ለአዳምና ለሔዋን ቃል ገባላቸው።

- እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል ገባላቸው።

- እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ ለሙሴና ለእስራኤላውያን ቃል ገባላቸው።

- እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ ለንጉሥ ዳዊትና ለንጉሥ ሰሎሞን ቃል ገባላቸው።

- እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል አልረሳም።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ያላመኑ ቢሆኑም እንኳን እግዚአብሔር አዳኙን ላለመላክ ወስኗልን?

- አልወሰነም።

-እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ያላመኑ ቢሆኑም እንኳን እግዚአብሔር አሁንም አዳኝ ለመላክ የፈለገው ለምንድን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ስለሚወድ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ለማዳን ስለሚፈልግ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ማንም ሰው ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር እንዲሄድ ስለማይፈልግ ነው።

- እግዚአብሔር ስለ ሚመጣው አዳኝ መልእክቱን ያስታላለፈው ለማን ነበር?

- ለነቢያት።

- ስለ አዳኙ መምጣት እግዚአብሔር ለነቢያት የተናገረው መልእክት የሚገኘው የት ነው?

- በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ።

- እግዚአብሔር አዳኙን ከመላኩ በፊት በአዳኙ ላይ የሚደርሰውን ነገር ሁሉ አስቀድሞ ዐቅዷል።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ምን አለ?

ኢሳይያስ 9፡7

7- ለመንግሥቱ ስፋት፣ ለሰላሙም ብዛት ፍጻሜ የለውም፤ ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣ መንግሥቱን በፍትሕና በጽድቅ ይመሠርታል፤ ደግፎ በመያዝም ያጸናዋል። በዳዊት ዙፋን ይቀመጣል፤ አገሩንም ሁሉ ይገዛል።

- እግዚአብሔር አዳኙ ከዳዊት ዘር እንደሚሆንና ለዘላለም እንደሚነግሥ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን አለ?

ኢሳይያስ 7፡14

14- ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፤ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።

- እግዚአብሔር አዳኙ የሰው አባት ወይም እናት ዘር አይኖረውም ነገር ግን ከድንግል ይወለዳል አለ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ሚክያስ 5፡2

2- «አንቺ ግን፣ ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፤ ከይሁዳ ነገዶች መካከል ትንሿ ብትሆኚም፣ አመጣጡ ከጥንት፣ ከቀድሞ ዘመን የሆነ፣ የእስራኤል ገዥ፣ ከአንቺ ይወጣልኛል።»

- እግዚአብሔር አዳኙ በቤተልሔም ከተማ እንደሚወለድ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ሆሴዕ 11፡1

1- «እስራኤል ገና ሕፃን ሳለ ወደድሁት፤ ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት።»

- እግዚአብሔር አዳኙን ከግብፅ እንደሚጠራው ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ኢሳይያስ 11፥2

2 - የእግዚአብሔር መንፈስ፤ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ፣ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል።

- እግዚአብሔር አዳኙ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ኢሳይያስ 53፥4-5

4- በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤ እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፣ እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተሠቃየም ቈጠርነው።

5- ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።

- እግዚአብሔር አዳኙ ለሰዎች ብሎ መከራ እንደሚቀበል ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

መዝሙር 41፥9

9- እንጀራዬን ተካፍሎኝ የበላ፣ የምተማመንበትም የቅርብ ወዳጄ፣ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።

- እግዚአብሔር አዳኙን ከወዳጆቹ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠው ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ዘካርያስ 11፡12-13

12- እኔም፣ «የሚበጅ መስሎ ከታያችሁ ዋጋዬን ክፈሉኝ፤ አይሆንም ካላችሁም ተውት» አልኋቸው፤ ስለዚህ ሠላሳ ብር ከፈሉኝ።

13- እግዚአብሔርም ሊከፍሉኝ የተስማሙበትን ጥሩ ዋጋ «በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኑረው» አለኝ፤ እኔም ሠላሳውን ብር ወስጄ በእግዚአብሔር ቤት ባለው ግምጃ ቤት አስቀመጥሁት።

- እግዚአብሔር አዳኙ በሠላሳ ብር እንደሚሸጥ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

መዝሙር 27፡2

2- ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ፣ ክፉዎች ገፍተው በመጡ ጊዜ፣ ጠላቶቼና ባላጋራዎቼ በተነሲብኝ ጊዜ እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ።

- እግዚአብሔር አዳኙ በሐሰት እንደሚከሰስ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ኢሳይያስ 50፥6

6- ለሚገርፉኝ ጀርባዬን፣ ጢሜን ለሚነጩ ጕንጩን ሰጠሁ፤ ፊቴን ከውርደት፣ ከጥፋትም አልሰወርሁም።

- እግዚአብሔር አዳኙን ሰዎች እንደሚመቱትና እንደሚተፉበት ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ኢሳይያስ 53፥7

7- ተጨነቀ፣ ተሠቃየም፤ ነገር ግን አፉን አልከፈተም፤
እንደ ጠቦትም ለዕርድ ተነዳ፤ በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ፤ አፉን አልከፈተም።

- እግዚአብሔር አዳኙ በሚከሰስበት ጊዜ ምንም ነገር አይናገርም አለ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ኢሳይያስ 53፥3

3- በሰዎች የተናቀና የተጠላ፣ የሕማም ሰውና ሥቃይ
ያልተለየው ነበር። ሰዎች ፊታቸውን እንደሚያዞሩበት ዐይነት፣
የተናቀ ነበር፤ እኛም አላከበርነውም።

- እግዚአብሔር ሰዎች አዳኙን እንደማይቀበሉት ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

መዝሙር 69፡4

4- ያለ ምክንያት የሚጠሉኝ፣ ከራሴ ጠጕር በዙ፤ ሕይወቴን ለማጥፋት የሚፈልጉ፣ በከንቱም የሚጠሉኝ ብዙዎች ሆኑ።

- እግዚአብሔር አዳኙ ያለአንዳች ምክንያት እንደሚጠላ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

መዝሙር 22፡16

16- ውሾች ከበቡኝ፤ የክፉዎች ሸንጎ በዙሪያዬ ተሰልፎአል፤ እጆቼንና እግሮቼንም ቸነከሩኝ።

- እግዚአብሔር አዳኙ እጆቹና እግሮቹ እንደሚቸነከሩ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

መዝሙር 22፡18

18- ልብሶቼን ተከፋፈሉ፤ በእጀ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።

- እግዚአብሔር ሰዎች በአዳኙ ልብሶች ላይ ዕጣ እንደሚጣጣሉ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

መዝሙር 22፡6-7

6- እኔ ግን ትል እንጂ ሰው አይደለሁም፤ ሰው ያላገጠብኝ፣ ሕዝብም የናቀኝ ነኝ።

7- የሚያዩኝ ሁሉ ይሣለቁብኛል፤ ራሳቸውንም እየነቀነቁ እንዲህ እያሉ ይዘልፉኛል።

- እግዚአብሔር አዳኙ እንደሚፌዝበትና እንደሚሰደብ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ኢሳይያስ 53፡12

12- ስለዚህ ድርሻውን ከታላላቆች ጋር እሰጠዋለሁ፤ ምርኮውን ከኀያላን ጋር ይካፈላል። እስከ ሞት ድረስ ሕይወቱን አሳልፎ በመስጠቱ፣ ከክፉ አድራጊዎችም ጋር በመቈጠሩ፣ የብዙዎችን ኃጢአት ተሸከመ። ስለ ዐመፀኞችም ማለደ።

- እግዚአብሔር አዳኙ ከክፉ ሰዎች ጋር እንደሚሞት ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

ኢሳይያስ 53፥9

9- በአፉ ተንኰል ሳይገኝበት፣ ምንም ወንጀል ሳይሠራ፣ አሟሟቱ ከክፉዎች፣ መቃብሩም ከባለጠጎች ጋር ሆነ።

- እግዚአብሔር አዳኙ ከባለጠጎች ጋር እንደሚቀበር ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

መዝሙር 16፥10

10- በሲኦል ውስጥ አትተውኝምና፤ ቅዱስህም መበስበስን እንዲያይ አታደርግም።

- እግዚአብሔር አዳኙ ከሞት እንደሚነሣ ተናገረ።

- እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ሌላስ ምን ተናገረ?

መዝሙር 68፥18

18- ወደ ላይ ዓረግህ፤ ምርኮ አጋበስህ።

- እግዚአብሔር አዳኙ ወደ ሰማይ እንደሚመለስ ተናገረ።

- እግዚአብሔር አዳኙን ከመላኩ በፊት በአዳኙ ላይ የሚደርሰውን ነገር ሁሉ አስቀድሞ ዐቅዷል።

- የእግዚአብሔር ነቢያት እግዚአብሔር ስለሚልከው አዳኝ ለእስራኤላውያን ተናገሩ።

- የእግዚአብሔር ነቢያት እስራኤላውያን የኃጢአትን መንገድ ትተው የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ ነገሯቸው።

- አብዛኛዎቹ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ነቢያት የተናገሩትን መልእክት ሰምተዋል?

- አልሰሙም።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ነቢያት ላይ ምን አደረጉባቸው?

- ገደሏቸው።

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ነቢያት የገደሏቸው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም የእግዚአብሔር ነቢያት እስራኤላውያን የኃጢአትን መንገድ ትተው የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ ስለ ነገሯቸው ነው።

- ምክንያቱም የእግዚአብሔር ነቢያት ለእስራኤላውያን እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን በሞት እንደሚቀጣ ስለነገሯቸው ነው።

- ምክንያቱም እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ስለ ወደዱና እግዚአብሔርን መታዘዝ ስላልፈለጉ ነው።

- የእግዚአብሔርን ነቢያት ከመስማት ይልቅ እስራኤላውያን ማንን ሰሙ?

- ሐሰተኞችን ነቢያት።

- ሐሰተኞቹ ነቢያት የእግዚአብሔር ነቢያት እንደሆኑ ቢናገሩም ነገር ግን እነርሱ የሰይጣን ነቢያት ናቸው።

- ሐሰተኞቹ ነቢያት እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን እንደማይቀጣ ይናገሩ ነበር።

- ሐሰተኞቹ ነቢያት እነርሱ የእግዚአብሔርን እውነት እንደሚናገሩ ገለጹ የተናገሩት ግን ምን ነበር?

- የተናገሩት የሰይጣንን ውሸት ነበር።

- በሐሰተኞች ነቢያት የተናገረው ማን ነበር?

- ሰይጣን።

- ዛሬም ሰይጣን ውሸቱን በሰዎች አማካይነት መናገሩን ቀጥሏል?

- አዎን።

- ሰይጣን ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይከተሉ በሰዎች አማካይነት ይናገራል።

- ሰይጣን ሰዎች ከዘር የመጣውን መናፍስት እንዲያመልኩ በሰዎች አማካይነት ይናገራል።

- ሰይጣን ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይሰሙ በሰዎች አማካይነት ይናገራል።

- ሰይጣን የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንዳልሆነ በሰዎች አማካይነት

ይናገራል።

- ሰይጣን እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደማይቀጣ በሰዎች አማካይነት ይናገራል።

- እስራኤላውያን የቀረጿቸውን ምስሎች እያመለኩ፥ እግዚአብሔርንም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ማምለክ ቀጥለው ነበር?

- አዎን።

- እስራኤላውያን የቀረጿቸውን ምስሎች እያመለኩ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለእርሱ ያቀርቡ የነበረውን አምልኮ እግዚአብሔር ተቀብሏል?

- አልተቀበለም።

- እስራኤላውያን የቀረጿቸውን ምስሎች እያመለኩ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለእርሱ ያቀርቡ የነበረውን አምልኮ እግዚአብሔር ያልተቀበለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም አምልኮአቸው የከንፈር እንጂ ከልብ ያለመሆኑን እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው።

- ምክንያቱም የተቀረጹ ምስሎችን ከልብ እንደሚያመልኩ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው።

- ስለ ልባችን ሁሉን ነገር የሚያውቅ ማን ነው?

- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር በልባችን ያለውን ነገር ሁሉ ያያል።

- እግዚአብሔር እርሱን እያመለክነው ያለነው ከልባችን ይሁን ወይም ከአፋችን ያውቃል።

- እግዚአብሔር ስለ ልባችን ምን ይላል?

- እግዚአብሔር ልባችን ሁሉ በኃጢአት መሞላቱን ይናገራል።

- ምንም እንኳን አብዛኞቹ እስራኤላውያን ለተቀረጹ ምስሎች ቢሰግዱም እግዚአብሔርን ብቻ የሚያመልኩ እስራኤላውያን ነበሩ?

- አዎን።

- ጥቂቶች ነበሩ።

- እግዚአብሔርን ብቻ የሚያመልኩት እስራኤላውያን ማንን ይጠብቁ ነበር?

- እነርሱ አዳኝ እንዲልክላቸው እግዚአብሔርን ይጠባበቁ ነበር።